# ደሮ ለማዳን ሙክት አይታረድላትም!

ባለፈው ወር አካባቢ በግንቦት 7 ድርጅት አማካይነት በወጣው መግለጫ ተንተርሶ በትግርኛ ተናጋሪው ኢትዮጵያዊ ያነጣጠረ ማለትም እንደሌላው ወገኑ ፀረ መንግስት ትግል ሲያካሄድ አይታይም የሚል እንድምታ ያለው በመገናኛ ብዙሃን ሲነገርና ባንዳንድ ድህረ ገፆችም ተጽፎ አንብቤለሁ። የዲያስፖራው ፖለቲካ በዘፈቀደ የሚሄድና ራዕይ የጎደለበት በመሆኑ ብዙ ባይገርመኝም፣ ይህ አባባል ግን መስመር ያለፈና ውስጠ-በቀል ያለው መልዕክት በመሆኑ ይህችን እንድል ተገድጃለሁ።

በመጀመርያ ትግል ማለት ምንድነው ከሚለው ለመነሳት መርጫለሁ። እኔ እስከማውቀው በኢትዮጵያ ምድር ኢህአፓና ወያኔ ሲታገሉ አውቃለሁ። ችግርና መከራ እየተቀበሉ ላመኑበት ቁመው ደም የከፈሉ እነሱ ናቸው። ከዚሁ በመለስ ያለው የዲያስፖራው ትግል ግን ለስሙ ካልሆነ በስተቀር በተግባር ያንን ያህል ያመጣው ለውጥ የለም። እንዲያውም ከጥቅሙ ጉዳቱ ሚዛን የደፋበት ሁናቴ አስከትላል ለማለት ያስደፍራል። ልክ ያለው መንግስት እንደሚያደርገው ህዝቡን እየከፋፈሉት ነው ለማለት ይቻላል። በኔ እምነት ስሙ ተቃዋሚ ይባል እንጂ ተግባሩ ባፉ ከሚያወግዘው መንግስት የተለየ ሁናቴ አይታይበትም ባይ ነኝ።

አሁን እስኪ ስለትግራይ ተወላጆች እኩል ሲታገሉ አይታዩም የሚለው ለጊዜው ልተወውና እስኪ ትግል እያካሄድን ነው ወደ ሚሉ ሰዎች እንሸጋገር። በመጀመርያ ደረጃ የድርጅት መሪ ነን የሚሉ እርስ በርሳቸው የማይግባቡ፣ በቅራኔና በቂም የተዋጡ ናቸው። ከዚያም አልፎ የአላማ ፅናት የሌላቸውና የግል ጥቅም የሚያስቀድሙ ናቸው። በአጠቃላይ ካገር ቤት ውጭ ያለው ህዝብ ተሰባስቦ ላገሩ የሚችለውን እንዳያደርግ እንቅፋት የሆኑ የዘመኑ መናፍቃን ናችው። እና ለሌላው ወገን ስም ለመስጠት ፍጹም የሞራል ብቃት የሌላቸው መሆኑን መታወቅ አለበት።

የብዙሃኑ ህዝብ ጉዳይ ሲነሳ ላብነት የዲሲና አካባቢዋ ነዋሪው ኢትዮጵያዊ ልውሰድና ቁጥሩ እስከ መቶ ሺ ይደርሳል ይሉታል። ለሰለማዊ ሰልፍና ለሌላ አገራዊ ጉዳይ የሚወጣው ግን ቁጥሩ እጅግ አነስተኛ ነው። ከሁለት ወይም ሦስት መቶ ሰው አይበልጥም። ታድያ ለምንድነው ልክ እንደ ትግራይ ተወላጁ ህዝብ ስም እንደወጣለት **"ግዴታህ አትወጣም ያለኸው"** አልተባለም? ወይስ ይህ ህዝብ በማናውቀው ምስጥራዊ ትግል ውስጥ ገብቶ ግዴታውን እየተወጣ ስለሚገኝ ይህንን ስም ለሱ አይገባውም ነው?

ሌላው በተደጋጋሚ የሚሰማው ቃል "እኛ" ይህን እያረግን፣ እየፈጸምን ትግርኛው ተናጋሪው ግን…የሚለው ጉዳይ ማብራርያ ያስፈልገዋል። ለመሆኑ "እኛ" የሚሉት እንደሚገባኝ ከሆነ፣ ከትግርኛው ተናጋሪ ውጭ በሙሉ ያለው ኢትዮጵያዊ ያካተተ ቃል ይመስላል። እና እውነት ኦሮሞው ከእኛዎቹ አለ? ሌላው ብሄረሰብስ ከ"እኛ" ባዮቹ በውነት የተሰለፈ ነውን? ሌላው ይቅርና አማርኛ ተነጋሪው ባንድ ልብና እምነት የቆመ ነው? ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ ብለን ብናልፈው ይመረጣል።

ወደ ሌላ እውነታ እንሻገር። የአገራችን ህዝብ ብዛት 80-ሚልዮን-ነው-ይባላል።ከዚሁ- ከፍተኛ ቁጥር 4 ሚሊዮን (ትግርኛ ተናጋሪው) ወያኔን ይደግፋል እንበል። ለምን የቀረው ህዝብ እንደ ሚባለው ህብረቱ ካለው ያለውን መንግስት ማስወገድ አልቻለም? በትግርኛ ጥሩ አባባል አለ ለንዲህ አይነት ነገር ሲያጋጥም፣**”ወደንያ ከይሐምያስ ሰበይቲ ወደን የሓምያ”** ወደ አማርኛ ሲመለስ “ **ልጃቸውን እንዳያሙ የልጃቸው ምራት ያማሉ።”** አሁንም ተቓዋሚው ክፍል የሚመራበት ፍልስፍና አህያውን ፈርቶ ዳውላውን የሚለውን አይነት ነው። ማጠፍያ ሲያጥር የሌለውን አለ ብሎ ተቃዋሚው በትግርኛ ተናጋሪው የመሸማቀቅ ስሜትን ለመፍጠር የታለመ ይመስላል። ይህ ከሆነ መልእክቱ ደግሞ በዚሁ ተራ ነገር የሚደነግጥና የሚያፍር ያለ አይመስለኝም።

ወደ የትግራይ ተወላጆች እንደ ሌላው ወገናችው ሲቃወሙ አይታዩም ለሚለው ምን ማድረግ ነበረበት ይህ ህዝብ የሚል ጥያቄ ያስነሳል? እኔ እስከማውቀው ድረስ ከታንድ፣ ከሶሊዳሪትይና በቅርብ ደግሞ ዓረና የሚባል ድርጅት አቓቁሞ የታገለ ይገኛል። በተጨማሪም ከህብረ ድርጅቶች ከሚባሉ ከእንደነ ቅንጅትና ኢ.ድዩ ተሰልፎ የሚቻለውን እየፈጸመ ይገኛል። እና **እንደ ሌላው ወገን ሲታገሉ አይታዩም** የሚለው ምን ሲያደርግ ነው ከሌላው ወገኑ እኩል እየታገለ ነው የሚያስብለው ወይም የሚያሰኘው? እውነት አሁን ሌላው ወገን ከትግርኛ ተናጋሪው በላይ እየታገለ ነው የሚያስብለው ስራ ምንድነው የፈጸመው? እኔ እስከ ማውቀው አዎ በብዛት ራዲዮ ከፍተዋል፤ የግላቸው ምኞትና ህልም ሲነግሩን ቅዳሜና እሁድ ያልፋል። በድህረ ገጾችም የጥላቻና ስሜታዊ ነገር ያለበት በብዛት ይጽፋሉ። ያ ተግባር ትግርኛ ተናጋሪው ባለማድረጉ የተባለውን ስም የሚያሰጥ ከሆነ በዚሁ እስማማለሁ። አይ መልሱ ሌላ ነው የሚባል ከሆነ ደግሞ በዚሁ ዙርያ የጻፉና የተናገሩ ቢያስረዱን መልካም ነው እላለሁ። ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያካተተና ጠንካራ ድርጅት ተቓቁሞ ላገራችን የሚበጅ ሲሰራ እስካሁን አልታየም።ተቃዋሚው የሚባል ባገራችን ለውጥ ለማምጣት ከሚያጠፋው ጊዜ ይልቅ ርስ በርሱ ለመጠላለፍ የሚያባክነው ጊዜ ይበልጣል። ካገር ጉዳይ ይልቅ የግላቸው የስልጣን አጀንዳ የሚገዳቸው ናቸው። እና ከነዚህ ለምን አላዋልክም ወይም አልተሰልፍክም ተብሎ የትግራይ ተወላጆች የሚገባቸውን ፀረ መንግስት ትግል አላደረጉም ቢባል እሰየው ሺ ጊዜ ቢባልም መልካም ነው ባይ ነኝ። በጥላቻና በዘረኝነት የተወጠሩ የድርጅት መሪዎች በደነፉ ቁጥርና ከኛ ጋር ካልሆንክ የክርስትና ስም እናወጣለሃለን ባሉ ጊዜ የሚደነግጥ ህዝብ አለ ብለው የሚያስቡ ከሆነ እጅግ ተሳስተዋል። እናንተን በመከተልና በመምሰል አይደለም ለኢትዮጵያ የምንታገለው። ከናንተው ተሰልፎ ላገር ማሰብና መታገል የትም እንደማያደርስ  ያለፈው የ18 ዓመት ጉዞ በቂ ማስረጃ ነው።

ያለውን ስርዓት ለመለወጥ ያላማ ጽናትና ተደራጅቶ መታገልን ይጠይቃል። የድርጅት መሪዎችም የጎደላቸው ይህኑኑ ነው። ይህንን ድክመትና ጉድለት አምኖ ባዲስ መልክ ከመሄድ ይልቅ አሁን የተያዘው ፈሊጥ ቢኖር የሌላውን ጩሀት በመቀማት አርበኛ ለመሆን መሞከር ነው። እንዲሁ አይነት ተግባር ድሮም አልበጀም ለወደፊትም የሚያዋጣ አይመስለኝም። ይልቁንስ የሌላውን ስም ከማጉደፍ ራስን መፈተሽ በባህላችን ቢለመድ መከራችን ባጠረ ነበር።

ሌላው አንዳንድ ምሁራን የትግራይ ህዝብ ባለው ስርዓት ተጠቃሚ እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲገልፁ ይሰማሉ። ለናሙናም ስታስቲክስ ይዘው በሬድዮ ይጠቃቅሳሉ።

የሚያሳዝነው ግን ባማራና በኦርምያ አካባቢ የተሰሩ ማናቸውም የልማት ስራዎች ሲጠቅሱ ወይም ሲያወዳድሩ ግን አይሰሙም። በወያኔ ጥፋት ምክንያት የትግራይ ህዝብም አብሮ መደመርና እንደባዳ እንዲታይ ማድረግ የሚል የፖሎቲካ መሰርይነት የሆነ መልዕክት እንዳለው ለማንም ግልጽ ነው። እንዲህ አይነቱ ተግባር ደግሞ ያለው ስርዓት ሲያተርፍበት እንጂ የተበደልነው ኢትዮጵያውያን ሲጠቅመን አላየንም። ይህንኑ ነው ማመን ያቃተን።ከማንም በላይ በዚሁ መንግስት የተጎዳው ህዝብ ቢኖር ያው የትግራይ ህዝብ ነው። በዚሁ ስርዓት ተጠቃሚ ቢሆን ኑሮ በዋናው መዲናችን በብዛት ሲለምን ባልታየ ነበር።

አሁንም የማሰምርበት ነገር ቢኖር የትግራይ ህዝብ ለፍትህና ላገር አንድነት ከሌላው ወገኑ ተሰልፎ የታገለ ነው ያለው፤ ለወደፊቱም በዚሁ እንደማይታማ ያለፈው ታሪኩ ምስክር ነው።

በመጨረሻም አሁንም ደሮ ለማዳን ሙክት አይታረድላትም። ለጥቂት የስልጣን ጥመኞች አላማና ምኞት ሲባል በ$500.00 የአርበኝነት ምስክር ወረቀት አንገዛም። ባለመግዛታችንም በጅምላ ህዝብን ባልሆነ ነገር መፈረጅ ወንጀል ነው። ይልቁንስ ኢትዮጵያዊነት ክብርና እውነት ስለሆነ ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል እንዳሻን ባንመነዝረው መልካም ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!

ሃ/ደ